## የክትባት ፕሮግራም

- የሚኖሩት በየትኛውም ቦታ ቢሆን፣ ለህጻናት፣ በአስራዎቹ የእድሜ ከልል ውስጥ ለሚገኙ እና ለአዋቂዎች ክትባቶች ይሰጣል
- በየጊዜው የሚደረግ የሳንባ ነቀርሳ (TB) ምርመራ ያደርጋል።



## የትምህርት ቤት ጤና ፕሮግራም

- ለArlington Public Schools (APS) ተማሪዎች በትምህርት ቤት ክሊኒኮች ውስጥ የመጀመርያ ደረጃ የህክምና እርዳታ/ድንገተኛ ህክምና፣ የጆሮ እና የአይን ምመራዎች እና የጤና መረጃዎችን ይሰጣል።
- APS ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለመማር የሚያስፈልጉዎትን ነጻ ከትባቶች ይሰጣል። በትምህርት ቤት ውስጥ ለመከተብ ከትምህርት ቤቱ ነርስ ጋር ይገናኙ ወይም በስልክ ቁጥር 703-228-7444 ይደውሉ።
- APS ውስጥ ለመመዝገብ ሊያሟሏቸውየሚገቡ የጤና መስፈርቶችን ይገልጻል።
- በAPS የጤና ምርመራዎች፣ የመግቢያ መስፈርቶች እና ቅጾች መረጃ ለማግኘት፣ ይህን QR ኮድ ስካን ያድርጉ።



SCHOOL HEALTH
ARLINGTON PUBLIC HEALTH

# የምንሰጣቸው አገልግሎቶች እንዴት ሊያግዙዎት እንደሚችሉ ይወቁ

**የኛን ድረገጽ ይጎብኙ**

**www.arlingtonva.us/Public-Health**

**በስልክ ቁጥር 703-228-7444 ይደውሉ**

**ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም ቀጠሮ ለመያዝ ይደውሉልን።**

አብዛኛዎቹ አገልግሎቶች የሚያስከፍሉት በገቢ ላይ በመመስረት ነው።
Medicaidን እና Plan Firstን እንቀበላለን።
አብዛኛዎቹ አገልግሎቶች ቀጠሮ ያስፈልጋቸዋል።

ARLINGTON VIRGINIA
Public Health




## በውስጡ ምን አለ

- ክትባት
- የትምህርት ቤት ጤና
- የወላጅ/ጨቅላ ህጻን ትምህርት (PIE)
- ሴቶች፣ ጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት (WIC)
- የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች
  - የቤተሰብ ዕቅድ
  - በአስራዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ልጆች ጤና
  - በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች
- ሌሎች የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች

ግንቦት 2025 AMH

## የወላጅ እና የጨቅላ ህጻን ትምህርት (PIE) ፕሮግራም

የእድገት መዘግየት ወይም በአይነተኛ እድገት እና ትምህርት ላይ እክል የሚፈጥሩ የጤና ችግሮች ያሉባቸው ልጆች (0-3 ዓመት) ላሏቸው ቤተሰቦች ድጋፍ ያደርጋል።

- አካላዊ፣ ኦኩፔሽል፣ የንግግር፣የእድገት ህክምና እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ይሰጣል
- የቨርጂንያ የጨቅላ እና ህጻን ትስስር ክፍል (አስቀድሞ የሚሰጥ ድጋፍ)





## የሴቶች፣ ጨቅላዎች እና ህጻናት (WIC) ፕሮግራም

የሚከተሉትን በማቅረብ የነፍሰ ጡር ሴቶችን፣ በድህረ ወሊድ ወቅት የሴቶችን እና ጡት የሚያጠቡ ሴቶችን እንዲሁም የጨቅላ ህጻናትን እና ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናትን ጤና ለማሻሻል ያግዛል፥

- ነጻ ምግብ፣ የተመጣጠነ ምግብ አወሳሰድ ምክር እና ትምህርት
- የጡት ማጥባት ድጋፍ እና የኤሌክትሪክ የጡት ፓምፕ ብድሮች
- የክትባት ማጣርያዎች
- የጤና እና የማህበራዊ አገልግሎቶች ሪፈራል

እድሜያቸው ከ5 ዓት በታች ለሆኑ ህጻናት አባቶች፣ ጊዜያዊ ወላጆች እና ህጋዊ አሳዳጊዎች ማመልከት ይችላሉ።

## የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች

እነዚህ አገልግሎቶች የሚሰጡት በአንድ ክሊኒክ ውስጥ ነው። መኖርያዎ የትም ሆነ የት፣ በደስታ እንቀበልዎታለን። ሁሉም አይነት የጾታዊ ማንነት አገላለጾች ተቀባይነት አላቸው።

- በነጻ የሚሰጡ ኮንደሞችን ጨምሮ የወሊድ መቆጣጠርያ
- ድንገተኛ የወሊድ መቆጣጠርያ
- የእርግዝና ምርመራ
- የSTI ምርመራ እና ህክምና

### የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶች

በአስራዎቹ እድሜ ውስጥ ላሉ እና ልጆች ሊኖራቸው ለሚችል ሴቶች አገልግሎቶች ይሰጣል፥

- የሴቶች ምርመራዎች
- ፓፕ ስሚርስ/የሰርቪካል ካንሰር ምርመራ
- የማሞግራም/የጡት ምርመራ ሪፈራል

የቅድመ ግንዛቤ ምክር እና አገልግሎቶች ይሰጣል።

### በአስራዎቹ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ልጆች ጤና አገልግሎቶች

የወሲባዊ ጤና ትምህርትን እና የምክር አገልግሎትን ጨምሮ በአስራዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ ላሉ (ከ13-19 ዓመት) ልጆች አገልግሎቶች ይሰጣል።

### በግብረ ሥጋ/በወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች (STIs)

ኤምፖክስን እና ኤችአይቪን ጨምሮ STIs ላይ ምርመራ ያደርጋል፣ ያክማል፣ ያስተምራል።
እንደአስፈላጊነቱ ሪፈራል ይሰጣል።

## ሌሎች የማህበረሰብ ጤና አገልግሎቶች

### ተላላፊ በሽታዎች

ከሰው ወደ ሰው ወይም በአየር፣ በውሃ፣ በምግብ፣ በአፈር፣ በነፍሳት ወይም በእንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ያግዛል።

- አንድ አካባቢ ውስጥ ያሉ ሰዎች በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ በሽታ ሲያዙ በወረርሽኝ ክስተት ላይ ምርመራ ያደርጋል
- የጀርሞችን ስርጭት ለመግታት ወይም ፍጥነቱን ለመቀነስ የሚያግዝ መረጃ ይሰጣል

### የእንስሳት ንክሻ

በእብድ ውሻ በሽታ የመያዝ ስጋት መኖሩን እና በቀጣይ መደረግ ያለበት ምን እንደሆነ ለማወቅ በቤት እንስሳት ወይም በዱር እንስሳት ንክሻ ላይ ምርመራ ያደርጋል።

### ሰርሳሪ እንስሳትን/ፍልፈልን መቆጣጠር

በሰርሳሪዎች ችግሮች ላይ ትምህርት ይሰጣል ለምሳሌ እንዴት ማጽዳት፣ የምግብ ምንጮችን ማስወገድ እና የሰርሳሪዎች መኖርያዎች ማስወገድ ስለሚቻልበት ሁኔታ። የንብረት ባለቤቶች በንብረታቸው ላይ የተባይ መቆጣጠርያ ሊኖራቸው ይገባል።

### የመኪና ወንበር ክሊኒክ



የህጻናት የተሽከርካሪ ደህንነት ትምህርቶችን ይሰጣል። በገቢ ላይ በመመስረት በመከታተል ላይ ያሉና ብቁ የሆኑ የአርሊንግተን ነዋሪዎች ከ0-8 ዓመት ለሆናቸው ልጆች ነጻ የተሽከርካሪ ወንበር ወይም ቡስተር ያገኛሉ።